# “የመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ. ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 1/2018”

ታሕሳስ 11 ቀን 2018 ዓ.ም

**ማውጫ**

1. መግቢያ ..... 2
ክፍል አንድ ..... 3
ጠቅላላ ድንጋጌዎች ..... 3
2. አጭር ርዕስ ..... 3
3. ትርጓሜ ..... 3
ክፍል ሁለት ..... 3
የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ ..... 3
4. የኮሚቴው መቋቋም ..... 3
5. የኮሚቴ አባልነት መስፈርት ..... 3
6. የኮሚቴው ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ..... 4
7. የኮሚቴው ተጠሪነት ..... 4
8. የኮሚቴው የሥራ ጊዜ ..... 4
9. የኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነቶች ..... 4
10. የኮሚቴው አሠራር ሥርዐት ..... 5
11. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራትና ኃላፊነቶች ..... 5
ክፍል ሶስት ..... 5
የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት ..... 5
12. የቅድመ ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት ተግባራት ..... 5
13. ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ ሂደት ..... 5
14. ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የማቅረብ ሂደት ..... 6
15. ስለ የድምጽ መስጫ ወረቀት እና ሳጥን ..... 6
16. የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ..... 7
17. የድምፅ ቆጠራ ሂደት ..... 7
ክፍል አራት ..... 8
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ..... 8
18. የሌሎች ሕግጋት ተፈፃሚነት ..... 8
19. የጸደቀውን ደንብ በጥብቅ ስለመከተል ..... 8
20. የሚፀናበት ቀን ..... 8

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ፣ የማይክሮፋይናንስ ስራ አዋጅ ቁጥር 626/2009 (በአዋጅ ቁጥር 1164/2014 እንደተሻሻለ) እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያዘጋጀውን ረቂቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዕጩ ጥቆማ እና ምርጫ ሰነድን እንዲሁም በመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም የመመስረቻ ጽሁፍ መሰረት የማይክሮፋይናንሱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጠው መሾም ያለባቸው በመሆኑ፤

የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ግልጽነት የተሞላበት እና ህጋዊ ሂደቶችን የተከተለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት በማከናወን ታማኝ፣ ሀቀኛ፣ የአመራር ልምድና ክህሎት ያላቸው እና ተገቢውን ህጋዊ የብቃት መመዘኛ መስፈርት የሚያሟሉ ግለሰቦች የቦርድ ኃላፊነት እንዲይዙ ማድረግ ማይክሮፋይናንሱ ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራ ካለው የኩባንያ መልካም አስተዳደር መርህ አንጻር የግድ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ሰነድ እንደሚያመላክተው የማይክሮፋይናንስ ዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ሂደትን በበላይነት የሚመራ እና የሚቆጣጠር የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ አማካኝነት ስለሚቋቋምበት፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ጥቆማ ስለሚቀበልበት እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ስለሚያከናውንበት ሂደት እና አሰራር በግልፅ መመሪያ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 394 (2) እና በማይክሮፋይናንሱ መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 13.2.1 በተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ምርጫ ግልጽነት ተሞላበት እና ህጋዊ ሂደቶችን የተከተለ ለማድረግ ይህን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 1/2018 ዛሬ ታህሳስ 11 ቀን 2018 ዓ/ም ባካሄደው 2ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አፅድቋል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ የአሰራር መመሪያ "የመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ አፈጻጸም ደንብ ቁጥር 1/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ በሌላ አኳኋን ካልተተረጐመ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ያሉት ቃላት ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጓሜዎች ይኖራቸዋል፡-

3.1 **"ቦርድ"** ማለት የመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ ነው፡፡

3.2 **"ዋና ስራ አስፈፃሚ"** ማለት የመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሲሆን የማይክሮፋይናንሱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች በዋና ኃላፊነት የመምራት ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

3.3 **"ዳይሬክተር"** ማለት የማባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ነው፡፡

3.4 **"ሰራተኛ"** ማለት በመባዕ ማይክሮፋይናንስ ተቋም የተሾመ ወይም በስራ ቅጥር ውል አማካኝነት የተቀጠረ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ከፍተኛ ሥራ አመራር ወይም የማይክሮፋይናንሱ የዕለት ከዕለት ሥራዎችን የሚያከናውን ማናቸውም ሰው ነው፡፡

3.5 **"ጠቅላላ ጉባዔ"** ማለት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ እና/ወይም መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ማለት ነው፡፡

3.6 **"ተጽእኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮን"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጠቅላላው የማህበሩ የተፈረመ አክሲዮን ውስጥ 2% (ሁለት በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ ድርሻ የያዘ ሰው ማለት ነው፡፡

3.7 **"ተጽእኖ ፈጣሪ ያልሆነ ባለአክሲዮን"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጠቅላላው የመባዕ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ. የተፈረመ አክሲዮን ውስጥ ከ2% (ሁለት በመቶ) በታች የአክሲዮን ድርሻ የያዘ ሰው ማለት ነው፡፡

3.8 **"ኮሚቴ"** ማለት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ ነው፡፡

3.9 **"የብቃት መመዘኛ"** ማለት ብሔራዊ ባንክ የማይክሮፋይናንስ ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላትን በሚመለከት በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ተፈላጊ የትምህርት፣ የሥራ ልምድ፣ የብቃት፣ የተገቢነት እና የሥነ ምግባር መመዘኛ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ

### 4. የኮሚቴው መቋቋም

4.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በሚከናወንበት የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይቋቋማል፡፡

4.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው 5 (አምስት) አባላት ይኖሩታል፡፡

4.3 የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴነት የሚጠቆሙ እጩዎችን በመቀበል ለእያንዳንዱ እጩ በቅደም ተከተል ድምፅ እንዲሰጥበት በማድረግ 5 (አምስት) እጩዎችን የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት እንዲሆኑ በድምፅ ብልጫ ይመርጣል፡፡

### 5. የኮሚቴ አባልነት መስፈርት

5.1. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው አባል በመሆን የሚመረጥ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

5.1.1. የማይክሮፋይናንሱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም ሰራተኛ ያልሆነ፣

5.1.2. የማይክሮፋይናንሱ ባለአክሲዮን የሆነ/ሆነች፣

5.1.3. በጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባልነት ለመሥራት ፍላጐት ያለው/ያላት፣

5.1.4. የማይክሮፋይናንሱ ሰራተኛ ያልሆነ/ች፣

5.1.5. ቢያንስ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ወይም የዚህን ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት ያጠናቀቀ/ች፤

5.1.6. የሕዝብን ጥቅም ከእምነት ማጉደል ወይም ከማጭበርበር ድርጊት ለመጠበቅ ሲባል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የወጡ ማንኛውንም ሕጎች በመተላለፍ በወንጀል ጥፋተኛ ያልተባለ/ች ወይም ሪኮርድ እና ማስረጃ የሌለበት/ባት፡፡

5.2. ከጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው አባላት መካከል ቢያንስ ሁለቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ያልሆኑ ባለአክሲዮኖች ሊሆኑ ይገባል፡፡

## 6. የኮሚቴው ሰብሳቢ እና ጸሐፊ

6.1. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው አባላት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ከተመረጡ በኋላ ወዲያውኑ ተሰብስበው በድምጽ ብልጫ የኮሚቴውን ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ይመርጣሉ፡፡

6.2. የኮሚቴው ሰብሳቢ ኮሚቴውን የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡ በዚሁ መሰረት ስብሰባዎችን የመጥራትና አጀንዳዎችን የማዘጋጀት እንዲሁም ኮሚቴውን በመወከል ከባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ እና ከዳይሬክተሮች ቦርድ ጋር ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

6.3. የኮሚቴው ፀሐፊ የሁሉንም ስብሰባዎች እና ውሳኔዎች ሂደት የሚያሳይ ቃለጉባዔ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡፡ የስብሰባዎች ቃለጉባዔዎች ተይዘው፣ ቁጥር ተሰጥቷቸው በሁሉም የኮሚቴው አባላት ሊፈረምባቸው ይገባል፡፡

## 7. የኮሚቴው ተጠሪነት

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ነው፡፡

## 8. የኮሚቴው የሥራ ጊዜ

የዳይሬክተሮች ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው በተመረጠበት ጠቅላላ ጉባዔ ወዲያውኑ ሥራውን ማከናወን የሚጀምር ሲሆን የድምፅ ቆጠራው እስኪጠናቀቅ እና በብሔራዊ ባንክ ወይም በማናቸውም አካል ምርጫውን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰጥተው እስኪጠናቀቁ ድረስ በስራ ላይ ይቆያሉ፡፡

## 9. የኮሚቴው ተግባራትና ኃላፊነቶች

9.1. የዳይሬክተሮች ቦርድን የጥቆማ እና የምርጫ አፈጻጸም አጠቃላይ ሂደት የማከናወንና የመምራት ኃላፊነት አለበት፡፡

9.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በእጩነት የማቅረብ እና የማስመረጥ ሂደት አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በወጡ መመሪያዎችና በዚህ ደንብ መሰረት በግልፅነት፣ በፍትሐዊነት እና በታማኝነት መከናወኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

9.3. ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው የስራ ዘመኑ ሲጠናቀቅ የሰራቸውን ስራዎችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች ለቦርዱ ጽ/ቤት የማስረከብ ኃላፊነት አለበት፡፡

9.4. ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ጋር በተያያዘ ከባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ፣ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ ካምፓኒ ፀሐፊ እና የሥራ ኃላፊዎች ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

9.5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን በሚመለከት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ከሌሎች ተቋማት የሚነሱ ማናቸውንም ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ እና መፍትሄ ይሰጣል፡፡

9.6. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው አባላት አግባብነት ባላቸው የብሔራዊ ባንክ እና የባንኩ መመሪያዎች ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት ግልጽ፤ ሚዛናዊና ተቀባይነት ባለው አኳኋን ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት የሚደርስ ማናቸውም ጉዳት ካለ በተገቢው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 10. የኮሚቴው አሠራር ሥርዐት

10.1. ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን እና ስራዎቹን በጉባኤው ዕለት ያጠናቅቃል፡፡

10.2. ከጉባዔው መጠናቀቅ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው ስብሰባ ሊያከናውን ይችላል፡፡ በዚህም ወቅት ስብሰባው የሚከናውንበትን አጀንዳ፣ ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ሰብሳቢው ይወስናል፡፡

10.3. በኮሚቴው ስብሰባዎች ላይ ከጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት መካከል ከሶስት በላይ የሚሆኑት ሲገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

10.4. የኮሚቴው ውሳኔዎች የሚተላለፉት ከግማሽ በላይ በሚሆኑ የኮሚቴው አባላት ድጋፍ ሲያገኙ ነው፡፡ ሆኖም ግን በውሳኔ ሐሳቦች ላይ እኩል ድምፅ የተሰጠ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፉት የውሳኔ ሐሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

## 11. የዳይሬክተሮች ቦርድ ተግባራትና ኃላፊነቶች

11.1. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው የሚመራበትን ይህን ደንብ ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ ያጸድቃል፤

11.2. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት ምርጫን በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ ውስጥ በማካተት ያቀርባል፤

11.3. የዳይሬክተሮች ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት ምርጫ ሂደትን ያስፈጽማል፤

11.4. የፋይናንስ፣ የማቴሪያል እና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎችን ለጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ያቀርባል፤

11.5. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው አባላት በዚህ ደንብ እና ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ተገቢነት ባላቸው ሌሎች ህጎች እና መመሪያዎች ዙሪያ በዕለቱ በቂ የሆነ ግንዛቤ እንዲያገኙ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፡፡

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት</u>

## 12. የቅድመ ጥቆማ እና ምርጫ ሂደት ተግባራት

12.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ጠቅላላ ጉባኤ ከሚካሔድበት ቀን አስቀድሞ ምቹና የተሻለ የሆነ የግንኙነት ዘዴ በመጠቀም ባለአክሲዮኖች የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥቆማ ለማድረግ ሊከተሏቸው ስለሚገቡ ሂደቶች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት፡፡

## 13. ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ ሂደት

13.1. የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ በሚከናወንበት የባለክሲዮኖች ጉባዔ ላይ የዳይሬክተሮች ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ሰብሳቢ ከዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ መድረኩን በመረከብ ስንት እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በእጩነት መጠቆም እንደሚቻል፣ ተጠቋሚዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ ዝቅተኛ መስፈርቶችን፣ ጥቆማው በምን መልኩ እንደሚሰጥ እና ስለአጠቃላዩ የምርጫ ሂደት ለጠቅላላ ጉባኤው ማብራሪያ ከሰጠ በኋላ እጩዎችን የማቅረብ ሂደት መጀመሩን በመግለጽ ባለአክሲዮኖች እጩዎች እንዲጠቁሙ ይጋብዛል፡፡

13.2. በባለአክሲዮኖች የሚደረግ ጥቆማ የጠቋሚውን ባለአክሲዮን ማንነት የሚገለጽ እና የተጠቋሚውን ዕጩ ዳይሬክተር የትምህርት ደረጃ፣ የሞያ ብቃት እና የስራ ልምድ የተመለከተ አጭር ገለጻ ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡

13.3. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው በጉባኤው ወቅት እጩዎች ስም፣ ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፣ ያላቸውን ወቅታዊ የሥራ ኃላፊነት በመግለጽ ለጠቅላላው ጉባኤ እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ እና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ለመሥራት ያላቸውን ፍላጎት እንዲገልፁ ያደርጋል፡፡

13.4. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ከአንድ በላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በእጩነት መጠቆም አይችልም፡፡ የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ አባላት ለቦርድ አባልነት ሊጠቆሙ አይችሉም፡፡ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን እራሱን በእጩ ዳይሬክተርነት መጠቆም ይችላል፡፡

13.5. በእጩነት የተጠቆመው ባለአክሲዮን ሕጋዊ ሰውነት ያለው በሚሆንበት ጊዜ፤ ይህን ተቋም የሚወክለው የተፈጥሮ ሰው በጥቆማው ወቅት ተለይቶ በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ለዳይሬክተሮች ቦርድ የተቀመጡ የብቃት መመዘኛ

መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ በጥቆማው ወቅት የተቋሙን ተወካይ መለየት ያልተቻለ እንደሆነ ተቋሙ በሂደት ለዳይሬክተሮች ቦርድ የተቀመጡ የብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን የሚያሟላ የቦርድ አባል ይመድባል፡፡

## 14. ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የማቅረብ ሂደት

14.1. የብሔራዊ ባንክ የተገቢነት እና የብቃት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው በቂ ተጠቋሚ እስከሚገኝ ድረስ በተጠቋሚዎች ላይ የሚነሳ ተገቢነት ያለው እና በማስረጃ የተደገፈ ተቃውሞ እና ድምፀ ተአቅቦ እስከሌለ ድረስ እያንዳንዱን ተጠቋሚ ይቀበላል፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ ተጠቋሚዎች እኩል ድምፅ ያገኙ እንደሆነ የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድ፤ የፆታ ስብጥር እና ሌሎች ተገቢነት ያላቸውን መሥፈርቶችን ከግምት በማገባት ዕጩውን ይመርጣል፡፡

14.2. ኮሚቴው በጠቅላላ ጉባዔው የተጠቆሙ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ በእጩነት የቀረቡ እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ያካተተ የእጩዎች ዝርዝር በማዘጋጀት ለጉባዔው ያቀርባል፡፡

14.3. ኮሚቴው በሚያዘጋጀው የዕጩዎች ዝርዝር (list of nominees) ላይ ለቦርድ አባልነት እጩ ሆነው ከሚቀርቡት አባላት መካከል፡-

14.3.1. 1/3ኛ የሚሆኑት ተጽእኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች መጠቆማቸውንና መመረጣቸውን፤

14.3.2. 1/3ኛ የሚሆኑት በሁሉም ባለአክሲዮኖች መጠቆማቸውንና መመረጣቸውን፤

14.3.3. ከላይ በተገለፀው መሰረት የሚዘጋጀው የዳይሬክተሮች እጩ ዝርዝር (list of nominees) ውስጥ ሴቶች የዳይሬክተሮች ቦርድ እጩ ሆነው እንዲጠቆሙ እና በእጩነት እንዲቀርቡ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

14.4. ማይክሮፋይናንሱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ባለአክሲዮኖች የሌሉት እንደሆነ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 14.3 ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚነት የለውም፡፡ እንዲህ ባለው ጊዜ ኮሚቴው፥ **የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት** ተለይተው ለተቀመጡ የቦርድ መቀመጫዎች ሁለት የዕጩ ዳይሬክተሮችን ዝርዝር በማዘጋጀት ሁሉም ባለአክሲዮኖች ድምጽ እንዲሰጡበት ለጉባዔው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

14.5. ለዕጩ የቦርድ አባልነት ከተጠቆሙት ውስጥ ለቦርድ አባልነት ምርጫ በእጩነት የሚቀርቡት ሰዎች ብዛት ለእያንዳንዱ በንዑስ አንቀጽ 14.3 ለተጠቀሰው የቦርድ አባላት መደብ ቢያንስ እጥፍ መሆን አለበት፡፡

14.6. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው እጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን በዚህ አንቀፅ 13.1 መሰረት ባለአክሲዮኖች እንዲጠቁሙ አሳውቆ የተጠቆሙ እጩ ዳይሬክተሮች የሌሉ እንደሆነ ወይም የተጠቆሙት እጩዎች ከሚፈለገው ቁጥር በታች ከሆነ ወይም የተጠቆሙት እጩዎች ህጋዊ የብቃት መመዘኛ መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆኑ፣ የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ተገቢውን የብቃት መመዘኛ መስፈርት የሚያሟሉ የራሱን እጩዎች ዝርዝር ፍትሀዊነትን፤ ግልፅነትን እና አስተማማኝነቱን ከሚያሳይ መግለጫ ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፡፡

14.7. ከእጩዎቹ መካከል ማንኛውም ሰው በቦርድ አባልነት ለመመረጥ ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ተቀባይነት ካላገኘ፣ ቀሪ ዕጩዎች ተተኪ ዕጩ የቦርድ አባል ሁነው በጉባዔው ወይም ዳይሬክተሮች በማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ተጠቁመው ለምርጫ ይቀርባሉ፡፡

## 15. ስለ የድምጽ መስጫ ወረቀት እና ሳጥን

15.1. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ ሂደትን ከጉባኤው ሰብሳቢ፣ ድምፅ ቆጣሪዎችና የማህበሩ ፀሀፊ ጋር በመተባበር የማካሄድ ኃላፊነት አለበት፡፡

15.2. የጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ከማህበሩ የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ባለአክሲዮኖች ድምፅ የሚሰጡባቸውን ድምፅ መስጫ ካርዶች/ወረቀቶችና እና የሚስጥር ድምፅ መስጫ ሳጥኖች (Secret ballots) ያዘጋጃል፡፡

15.3. የድምፅ መስጫው ወረቀት ቢያንስ ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

15.3.1. የባለአክሲዮኑ መለያ ቁጥር

15.3.2. የባለአክሲዮኑ ስም፣
15.3.3. በባለአክሲዮኑ የተፈረሙ አክሲዮኖች ብዛት፣
15.3.4. የስብሰባው ልዩ መለያ ቁጥር፣
15.3.5. የማይክሮፋይናንሱን ስም እና አርማ፣
15.3.6. የማይክሮፋይናንሱን ማህተም፤ እና
15.3.7. ለእያንዳንዱ የዕጩዎች ዝርዝር ባለአክሲዮኑ መምረጥ የሚፈልጋቸውን እጩዎች ስም የሚፅፍበት ስፍራ፡፡

15.4. የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ስለመገኘታቸው እንዲፈርሙ በሚደረግበት ወቅት ይሰራጫል፡፡

## 16. የድምፅ አሰጣጥ ሂደት

16.1. የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ በአንቀጽ 14.3 ወይም 14.4 መሠረት በኮሚቴው ለተያዙት እያንዳንዱ የዕጩ ዳይሬክተሮች ዝርዝሮች እና በዝርዝሩ ውስጥ ለተካተተው እያንዳንዱ እጩ ዳይሬክተር ድምጽ በመስጠት ይከናወናል፡፡

16.2. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ድምፅ መስጠት የሚችለው ለእያንዳንዱ የዕጩዎች ዝርዝር (list of nominees) በተፈቀደው የቦርድ አባላት ቁጥር ልክ ሆኖ በጠቅላላው ለ9 ዕጩዎች ብቻ ነው፡፡

16.3. ለእያንዳንዱ የዕጩዎች ዝርዝር ከተፈቀደው የቦርድ አባላት ቁጥር በላይ ወይም በጠቅላላው ከ9 (ዘጠኝ) እጩዎች በላይ ድምጽ የተሰጠ እንደሆነ ተቀባይነት የሚኖራቸው ተመራጮች በቅደም ተከተል ለእያንዳንዱ የእጩዎች ዝርዝር እስከ ተፈቀደው የቦርድ አባላት ቁጥር ድረስ ወይም እስከ 9ኛ ተራ ቁጥር ድረስ የተጠቀሱት ብቻ ይሆናሉ፡፡

16.4. ባለአክሲዮኖች በድምፅ መስጫዎቹ ላይ ሊመርጧቸው የሚፈልጓቸውን እጩ የቦርድ አባላትን ስሞች ወይም መለያ ቁጥር በመፃፍ ለምርጫው በተዘጋጁት የሚስጢር ሳጥኖች (Secret Ballots) ውስጥ ያስገባሉ፡፡

16.5. ባለአክሲዮኖች በግል ወይም በተወካያቸው አማካኝነት በጉባዔ በመገኘት ድምፅ መስጠት የሚችሉ ሲሆን አንድ ባለአክሲዮን የራሱን አክሲዮን አካትቶ ከጠቅላላው የተፈረመ ካፒታል ከ10% (አስር በመቶ) በላይ የሚሆነውን አክሲዮን በባለቤትነት የያዙ ባለአክሲዮኖችን ወክሎ ድምፅ መስጠት አይችልም፡፡

## 17. የድምፅ ቆጠራ ሂደት

17.1. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው ከጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ድምፅ ቆጣሪዎችና የማህበሩ ፀሀፊ እንዲሁም ከድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ጋር በመተባበር ድምፆቹን ይቆጥራል፡፡

17.2. ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው በእያንዳንዱ እጩ የተሰጠውን ድምፅ ብዛት እና ውድቅ የሚደረጉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት ይመዘግባል፡፡ አንዳንዶቹ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ውድቅ የተደረጉበትን ምክንያቶች በእያንዳንዱ ወረቀት ላይ በግልፅ በመፃፍ በጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ ተረጋግጦ ይፈረምበታል፡፡

17.3. አንድ ድምፅ መስጫ ወረቀት ውድቅ የሚደረገው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ይሆናል፡-

17.3.1. ድምፅ መስጫው ወረቀት የባለአክሲዮኑን ስም ያልያዘ ከሆነ፣
17.3.2. ድምፅ መስጫው ወረቀት በባለአክሲዮኑ የተፈረሙ አክሲዮኖች ብዛት የማይገልፅ ከሆነ፣
17.3.3. ድምፅ መስጫው ወረቀት የማይክሮፋይናንሱን ስም እና አርማ ያልያዘ ከሆነ፣
17.3.4. ድምፅ መስጫው ወረቀት የእጩው ስም ካልተፃፈበት፣
17.3.5. ድምፅ መስጫው ወረቀት ፊርማ ከሌለበት፣
17.3.6. ድምፅ መስጫው ወረቀት ስርዝ ድልዝ ካለበት ወይም ሰረዙ በፊርማ ያልተረጋገጠ ከሆነ፣
17.3.7. ድምፅ መስጫው ወረቀት የባለአክሲዮኑን መለያ ቁጥር ካልያዘ፣

17.4. ኮሚቴው በሚያከናውነው የድምጽ ቆጠራ ውጤት መሠረት ለእያንዳንዱ ዕጩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መደብ በተቀመጠው የአባላት ብዛት መሠረት ከፍተኛ ድምጽ ያገኙ ዕጩዎች የማይክሮፋይናንሱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

በመሆን ይመረጣሉ፡፡ የቦርድ አባል በመሆን ካልተመረጡ ዕጩዎች መካከል እንደቅደምተከተላቸው ለምርጫ በተወዳደሩበት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መደብ ስር አራት (4) እጩዎች በተጠባባቂነት ይያዛሉ፡፡

17.5. የድምፅ ቆጠራው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴው የድምፅ አሰጣጡንና የቆጠራውን ሂደት እንዲሁም የውጤቶቹን ተቀባይነት በተያዘው ቃለ-ጉባዔ እና ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ በመፈረም ያረጋግጣል፡፡

17.6. የተቆጠሩት ድምፆች ታሽገው ለብቻ ይያዛሉ፡፡

17.7. የድምፅ ቆጠራው ውጤት በዚያው ቀን ለጠቅላላው ጉባኤ ይገለፃል፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ውጤቱ በቀጣዩ የሥራ ቀን በማህበሩ ዋናው መ/ቤት የማስታወቂያ ሰሌዳ እንዲሁም በማይክሮፋይናንሱ ድረ ገጽ ላይ ይለጠፋል፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የሌሎች ሕግጋት ተፈፃሚነት

ይህንን የአሠራር ደንብ በማይሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተገቢነት ያላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና እንዲሁም የማህበሩ ፖሊሲ እና አሰራሮች እንደየሁኔታው እየታዩ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

### 19. የጸደቀውን ደንብ በጥብቅ ስለመከተል

የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማ እና ምርጫ ኮሚቴ በባለአክሲዮኖች የጸደቀውን ይህን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የምርጫ አፈጻጸም ደንብ በጥብቅ በማክበር የመሥራት ኃላፊነት አለበት፡፡

### 20. የሚፀናበት ቀን

ይህ ደንብ በባለአክሲዮች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ከፀደቀበት ታህሳስ 11 ቀን 2018 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡